

## የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የትምህርት ቤት የክትባት ፖሊሲ

### ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን ልጅዎ ክትባታቸውን በወቅቱ ማግኘታቸው አስፈላጊ ነው።

# ወደ መዋእለ ህጻናት እንኳን በደህና መጡ!

# ክትባቶችን የትምህርት መጀመሪያ የተግባር ዝርዝር ውስጥ ያድርጉ!

ሁሉም የዲሲ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ለመገኘት ክትባታቸው ላይ ወቅታዊ መሆን አለባቸው! የህጻንነት ክትባታቸውን ያልወሰዱ የመዋእለ-ህጻናት ተማሪዎች አስፈላጊውን ክትባቶች እስኪወስዱ እና ሰነዱን ለትምህርት ቤቱ እስኪሰጡ ድረስ በአካል ትምህርት ከማግኘት በጊዜያዊነት ይታገዳሉ።

**ልጅዎ ለመዋዕለ ህጻናት ዝግጁ እንዲሆን እነዚህን ሶስት እርምጃዎች አሁኑኑ ይውሰዱ!**

## 1

**የልጅዎን አመታዊ የደህንነት ጉብኝት ቀጠሮ ያስይዙ።**

የልጅዎን አመታዊ የደህንነት ጉብኝት ቀጠሮ ዛሬ ያስይዙ፣ እና የጤና አንክብካቤ አቅራቢዎ የUniversal Health Certificate (ዓለምአቀፍ የጤና ሰርተፊኬት) እንዲሞሉ ይጠይቁ። ልጅዎ በጉብኝቱ ወቅት ክትባቱን ከወሰደ፣ ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚያጋሩት የክትባቱን ማስረጃ በጽሁፍ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ።

## 2

**ልጅዎ ሁሉንም ክትባቶቻቸውን የወሰዱ መሆኑን ያረጋግጡ።**

ልጅዎ ሁሉም አስፈላጊ ክትባቶቻቸውን ስለመውሰዳቸው እርግጠኛ አይደሉም? ቀዳሚ የእንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ እና ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚያጋሩት የልጅዎን የክትባት ታሪክ ቅጂ ይጠይቁ።

## 3

**የክትባት ሰነዶቹ ለትምህርት ቤትዎ ያስረክቡ።**

ለመዋዕለ ህጻናት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የ Universal Health Certificate (የዓለምአቀፍ የጤና ሰርተፊኬት) እና ማንኛውም ሌሎች የክትባት ሰነዶች ለልጅዎ ትምህርት ቤት ያስረክቡ። ልጅዎ የሚያስፈልገውን ሁሉንም የክትባት ሰነዶች ያላቸው ስለመሆኑ እርግጠኛ አይደሉም? ትምህርት ቤቱ ጋር ይደውሉ እና ዛሬውኑ ይጠይቁ!

**ለተጨማሪ መረጃ፣**

**OSSE፣ (202) 727-6436 | DC Health: (202) 576-7130 | osse.dc.gov/immunization**

OSSE

DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR